# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፡፡

# Ethiopia: The Kingdom of God Services

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥ ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳት፥ የ"ኢትዮጵያ" እና "የኢትዮጵያውያን" የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ፡፡
To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God; and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.

ነሓሴ @4 ቀን፥ 09)(7 ዓ.ም.

ይድረስ፡-

ለዋኖስ፡ የኅትመትና የማስታወቂያ ድርጅት፤
መ. ሣ. ቁ. 04ሺ1)#፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡

በፈጣሪያችንና አምላካችን፥ ሊቀ ካህናታችንና ንጉሠ ነገሥታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በሃይማኖታችንና አገራችን፥ እናታችንና ንግሥታችን ድንግል ማርያም ስም ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን አቀርብላችኋለሁ፡፡

ከ"መለከት" ዝግጅት ክፍል፡ በባዕዳኑ አገዛዝ 24/10/97 በቁጥር ዋ.ኅ. መ.ድ. 544/97 እና ከዋናው ሥራ አስኪያጁ፡ ከአቶ ብርሃኑ ለማ፡ በዚሁ ቀን፡ በቁጥር 543/97 የጻፋችሁልኝ ደብዳቤዎች፡ ከግንቦት ወር፥ 09)(7 ዓ.ም. የመጽሔታችሁ ዕትምና ከሌሎች አባሪዎች ጋር ደርሰውኛል፡፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ፡፡

ይኸው መልእክታችሁ የደረሰኝ፡ በፍልሰታ ሱባዔ መግቢያ ሰሞን ስለነበረ፡ ወዲያው ይህን መልስ ልልክላችሁ ሳይቻለኝ ቀረ፡፡

አምላከ ኢትዮጵያ፡ የእርሱና የቅድስት እናቱ ታማኞች ልጆች ከኾኑት መካከል፡ እናንተን የመሰሉ፡ ጥሪውን የተቀበላችሁትን ጽኑዎች በማስነሣት፡ ዛሬ፡ ይኸው፡ የምትገኙበትን ሕይወት፡ እንዲህ፡ በማኅበር እንድትኖሩ፥ የምታካኺዱትንም ሥራ፡ እንዲህ፡ በኅብረት እንድትቀጥሉ አስችሎ፡ በዚሁ እንድትጠናከሩበት ማድረጉ፡ የአገራችንን፥ የሃይማኖታችንንና የወገናችንን ዘለዓለማዊ ህልውና በሚመለከት፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን፡ የገባልንን መለኮታዊ ቃል ኪዳኑን መጠበቁን አረጋግጦ ማሳየቱ ነው፤ ይህም፡ መስቀሉን ተሸክመን፡ በእርሱ መንግሥት አገልግሎት ለተጠመድነው፡ ለእኔና ለመሰሎቼ፡ የምሥራች ዜና ኾኖናል፤ ለዚህ ቸርነቱም፡ በፍጹም ደስታ ተመስጠን፡ ምስጋናችንን አቅርበንለታል፡፡ ሃይማኖታችሁን፡ በምግባር በመግለጽ፡ የፈጸማችሁትንና እየፈጸማችሁ ያላችሁትንም ግዳጅ ኹሉ ባርኮ፡ ለመልካም ፍሬ እንዲያበቃላችሁ እንጸልያለን፡፡

የፍጡራን ሕይወት፡ ከነተልእኮው፡ በወጣኒነት ተጀምሮና በማዕከላዊነት አልፎ፡ ለፍጹምነት ሊበቃ እንደሚገባው ታውቃላችሁ፤ እንዲህ ከኾነ፡ በዚህ ረገድ፡ እናንተ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ደርሳችሁበት ያለውን ማዕርግ ባላውቀውም፡ ወደመጨረሻው የፍጹምነት ደረጃ ለማምራት የምትችሉበትን መንገድ እንዳመላክታችሁ የፈቀዳችሁልኝ መኾናችሁን በማመንና ጥቃቅኑን በማስቀደም፡ አስተያየቴን፡ እነሆ፡ ባጭር ባጭሩ አቀርብላችኋለሁ፡፡

…2

መልእ. ሣ. ቁ. 8)02፤ ስልክ ቁ. 06-08-*5፤ "--*5፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡
P. O. Box 812, Tel. Nos. 16-18-85; 20-00-85, Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: ekogyesus@aol.com
Website: www.ethkogserv.org

ለደብዳቤዎቻችሁ መልስ ይኾን ዘንድ የላክሁላችሁ÷ እንደምክርም ልትቆጥሩት የምትችሉት፡ ይህ አስተያየቴ፡ በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ያዘጋጀሁት ስለኾነ፡ እናንተም፡ የጨለማን ሓሳት፡ በብርሃኗ አጋልጣ ታስወግደው ዘንድ፡ ፈጣሪያችን፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በየልቦናችሁ ቀርፆ ባኖራት፡ በመንፈስ ቅዱስ እውነት እንድትመለከቱት አደራ እላችኋለሁ::

1ኛ:- እግዚአብሔርንና እናት አገራችንን÷ ወገናችንንም የምንወድዳቸው መኾናችንን የምናረጋግጠው፡ የእነርሱ የኾነውንና ከእነርሱ ያገኘናቸውን ኹሉ፡ ከሌላው ይልቅ፡ አክብረንና ጠብቀን÷ አብልጠንና ቅድሚያም ሰጥተን የምንጠቀምባቸው ስንኾን ብቻ ነው:: እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ ምነው:-

ሀ. የደብዳቤዎቻችሁን ቀንና ቁጥር ለመለየት÷ የመልእክት ሣጥን÷ የዕትም ነጻብራቅና የስልክ ቁጥሮቻችሁንም ለመግለጥ የተጠቀማችሁት፡ የራሳችሁ በኾነው፡ በኢትዮጵያኛው፡ በግዕዙ ሳይኾን፡ እንዴትና ለምን፡ በባዕዳኑ እንዲኾን ወሰናችሁ፡ ልትቀጥሉበት ጨከናችሁ? ስለዚህ ነገር፡ ቀደም አድርጌ የጻፍሁላችሁ ስላለ፡ እዚህ ላይ፡ በመድገም፡ የእናንተንም÷ የእኔንም ጊዜ ማባከን አልፈቅድም::

ለ. "የኅትመትና የማስታወቂያ ድርጅት" የሚለውን ኢትዮጵያኛ ስያሜ፡ "Publishing & Advertising Enterprise" ወደሚለው፡ የባዕዳን ቃላት፡ በትክክለኛው የቋንቋ መልኩ ተርጉማችሁ ለማስቀመጥ ከቻላችሁ፡ Posters, Brochures, Cards & Lables, & Color Works ብላችሁ፡ በየራሳቸው ትክክለኛ መልካቸው የጻፋችኋቸውን ባዕዳን ቃላት፡ ያለመልካቸው፡ በኢትዮጵያኛው ፊደል፡ "ፖስተሮች÷ ብሮሽሮች÷ ካርዶች÷ ሌብሎችና የከለር ሥራዎች" ብላችሁ ከመጻፍ ይልቅ፡ በራሳቸው፡ ኢትዮጵያኛ መልካቸው፡ "ጽሑፍ ሰሌዳዎች÷ ዕትም መግለጫዎች÷ ክርታሶችና ተለጣፊ ምልክቶች÷ የመቀለም ሥራዎችም፤" ተብሎ እንዲጻፍ ማድረግ ትችሉ አልነበረምወይ?

2ኛ:- በደብዳቤአችሁ መግቢያ፡ የሰላምታ ማቅረቢያችሁ ላይ፡ "ምኞት እንጂ፡ ጸሎት የለንም!" በማለት የሠነዘራችሁት ኃይለ ቃል፡ ስለትሕትናም ቢኾን፡ በአንደበትም፡ ሊነገር÷ በጽሑፍም ሊሠፍር የሚገባው ስላልኾነ፡ በዝምታ ላልፈው አልተቻለኝም:: "ምኞት"፡ በምንም መልኩ፡ የአረማውያን÷ የአሕዛብ÷ የዓለማውያንና የሥጋውያን እንጂ፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን፡ ምናችንም አይደለም፤ በዚህ አንጻር፡ የእኛ የኢትዮጵያውያን፡ ዕድል ፈንታችንና ጽዋ ተርታችን፡ ጸሎት ነው፤ የምናመልከው ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ደግሞ፡ በምንም መልኩ፡ በፍጡራኑ መካከል፡ ልዩነትና አድልዎ አድርጎ፡ የማንንም ጸሎት "አልቀበልም!" የሚል አምላክ አይደለም:: እንዲያውም፡ የሚቀበለው፡ የተናቁትንና የተዋረዱትን÷ የተጠቁትንና ራሳቸውን፡ በትሕትና ዝቅ ያደረጉትን ሰዎች ጸሎት፡ መኾኑን እናውቃለን::

3ኛ:- "ከሞላ ጎደል" የተመለከታችኋቸውን መጻሕፍቴን፡ አሚልታችሁና ጨርሳችሁ እንደምታነብቧቸው ተስፋ አደርጋለሁ:: በእነዚያም ውስጥ፡ *"ያልገቡን አንዳንድ አንቀጾች አሉ፤ ለወደፊቱ፡ ፈቃደ እግዚአብሔር ቢኾን፡ የራሳችንን የተሳሳተ ግምት ሳንወስድ፡ ከምንጩ ጠይቆ መረዳት እንጂ፡ ሌላ አማራጭ እንደሌለው ስለምናምን፡ ማብራሪያ እንጠይቅ ይኾናል::"* ስትሉ በገለጻችሁት የእውነተኛነታችሁ ስሜት፡ ተደስቻለሁ፤ ምክንያቱም፡ ይህን የመሰለ፡ የእምነት አቋም ያለውና ይህንኑም አቋሙን፡ በሥራ ለመግለጽ የሚደፍር ሰው፡ በዚህ ትውልድ መካከል ለማግኘት ብርቅ ስለኾነ ነው:: ይኹን እንጂ፡ ከዚህ ጋር አያይዤ፡ "ፈቃደ እግዚአብሔር" ስለሚለው ዘይቤ ላሳስባችሁ የምወድደው፡ ይህንኑ፡ የእናንተን የመሰለውን፡ የእምነት አቋም፡ በምግባር እንዲገለጽ ለማድረግ ብቻ ሳይኾን፡ ሌላውም በጎ ነገር ኹሉ፡ ምንጊዜም፡ እንዲኾን፡ በእግዚአብሔር በኩል የተፈቀደ መኾኑን ነው፤ ይህም እውነታ፡ ገና ከአዳምና ሔዋን ጊዜ ጀምሮ ታውቆ፡ እስከክርስቶስ ድረስ፡ በነቢያቱ አንደበት ሲነገር የቆየ÷ በመጨረሻም፡ በራሱ፡ በክርስቶስ÷ ከእርሱ በኋላም፡ እስከዚች ቀን ድረስ፡ ለዘለዓለም፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ለኹሉ በገሃድ ተገልጦ፡ በቅዱሳን ጻድቃንና ሰማዕታት ሰውነት ላይ ሲሠራ÷ ፍሬም ሲያፈራ ኖርዋል::

አዎን! ፈቃደ እግዚአብሔርማ እንዲህ ኾኗል! እንዲህ ተሰጥቶአል፤ እንዲመጣልን፡ እንጠብቀውም፤ የሚቀረው፡ የእኛ፡ በእርሱ፡ የሃይማኖት ፍሬ የኾነውን ምግባር መፈጸም ብቻ ነው:: ስለዚህ፡ ባቀረባችሁት አሳብ መሠረት፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በሚመለከት፡ ማናቸውንም ዓይነት ጥያቄያችሁን ለመመለስ ደስ ብሎኝ እጠብቃለሁ::

4ኛ:- ከዚህ የእምነት አቋማችሁና የምግባር ይዘታችሁ የተነሣ፡ በተለይ ለእናንተና እናንተን ለመሰሉ፡ የኢትዮጵያ እውነተኞች ልጆች፡ በብርቱ ላሳስብ የምወድደው፡ ከኹሉ በፊት፡ ያለንበትን ዓለምና ዘመኑን፡ በትክክል እንድታውቁት ነው:: ያንም፡ ተደጋግሞ በሚነገረውና በሚደመጠው፥ በሚጻፈውና በሚነበበው ቃሉ፡ እግዚአብሔር፡ ላመኑበት፡ እውነተኞች ተከታዮቹ ኹሉ ግልጽ ስላደረገው፡ በዚህ ረገድ፡ ችግር እንደሌለ እገምታለሁ፤ ከዚህ የሚቀር ነገር ቢኖር፡ ከእውነተኞች አባቶችና እናቶች፥ መምህራንና መጻሕፍት በሚገኘው፡ ማሟላትና ማስተካከል ይቻላል:: እኔም፡ አኹን፡ በድርሻዬና በዓቅሜ እያደረግሁ ያለሁት፡ ይህንኑ ግዳጄን መወጣቴ መኾኑን እንድትገነዘቡልኝ እሻለሁ::

5ኛ:- ዛሬ፡ በሕይወተ ሥጋ ያለነው ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ልንፈጽመው ስለሚገባን ግዳጅ፡ ከቀደሙት መካከል፡ ምሳሌ የሚኾኑን፡ አያሌ ደጋግ ሰዎች እንዳሉን ታውቃላችሁ:: ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ያሉትን ቅዱሳን ነቢያትና ሓዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት ብንጠራቸው፡ ቍጥራቸው እጅግ ብዙ ነው:: ኹሉም፡ በጊዜያቸው፡ ግዳጃቸውን እየፈጸሙ ስላለፉ፡ እየራሳቸውን ለቅዱስነት አብቅተው፡ ለእኛም፡ እነሆ አብነት ኾነውናል:: ስለዚህ፡ ለዘመናችን ግዳጅ የተጠራነው ነቢያትና ሓዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት፡ እኛ፡ ሕያዋን ኾነን የምንንቀሳቀሰው፡ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት መኾናችንን፡ አበክረን ልንገነዘበው ይገባል:: ለአዛውንቱ፡ ምሳሌ የሚኾኑትን፡ ለጊዜው ልተዋቸውና፡ ለእናንተና እናንተን ለመሰሉት ወጣቶች፡ መልካም አርአያ ሊኾኑ ከሚገባቸው መካከል፡ ከአዲስ ኪዳኖቹ፡ ራሱን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፥ መጥምቁ ዮሓንስንና ዲያቆኑን እስጢፋኖስን፥ ከብሉይ ኪዳኖቹ ደግሞ፡ ዳንኤልን፥ አናንያን፥ አዛርያስንና ሚሳኤልን እጠቅሳቸዋለሁ::

በእግዚአብሔር አገርነቷ፥ ሕዝብነቷና መንግሥትነቷ፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን አንድ አድርጋ የምታስተዳድረዋን፡ እናት አገራችንን ኢትዮጵያን፡ "እንወድዳታለን!" ካልን፡ ዛሬ፡ እያንዳንዳችን፡ ስለእግዚአብሔር እውነት ቆመን፡ በዘመናችን የኾነውና እየኾነ ያለው ኹሉ፡ የደረሰው ያለበቂ ምክንያት አይደለምና፡ ያን ምክንያት አውቀን፡ ጌታችንና ስማቸው፡ ከላይ የተጠቀሰው ቅዱሳን ጀግኖች ለፈጸሙት ግዳጅ፡ እየራሳችንን ማብቃት አለብን:: እነዚያ ቆራጦች ሰማዕታት፡ የነበሩበት ዘመን እኮ፡ ልክ፡ ዛሬ፡ እኛ ያለንበትን የሚመስል እንደነበረ ለመገንዘብ፡ ለማነኛችንም የሚያዳግት አይመስለኝም::

በእነዚያ ዘመን እንደኾነው ኹሉ፡ ዛሬም፡ ሰዎች፡ በአገራችን፡ ከእግዚአብሔር ሥርዓት ይልቅ፡ የራሳቸውን ጥቅምና ክብር እንዲጠብቅላቸው የሠሩት፡ የየራሳቸው ሥርዓት፡ ጸንቶ እንዲቀጥል ይፈልጋሉ:: ውድቀትንና ጥፋትን ያመጣውና የሚያመጣውም፡ ይህን የመሰለው የተሳሳተ አካኼድ መኾኑን፡ እኒያ ጀግኖች ስላወቁ፡ ዓለምንና ወገናቸውን፡ ከመደምሰስ ለማዳን ሲሉ፡ ስለእግዚአብሔር ሥርዓት፡ እውነትን በመናገር፡ እየራሳቸውን፡ መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ! ስለዚህ፡ ዓለምና ወገናቸው፡ ከመደምሰስ ተርፎ፡ ዛሬ፡ እኛን ያስገኘው፡ ይህ ትውልድ፡ በህልውናው ሊቀጥል ቻለ::

እንግዲህ፡ የምትወድዷት አገራችሁና ወገናችሁ፡ በሰዎች ሳይኾን፡ በእግዚአብሔር ሥርዓት እንዲቀጥሉ፡ በእውነት ከፈለጋችሁ፡ ማንንም ሳትፈሩ፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ ያለፍርሃት በግልጽ እየተናገራችሁ፡ እንደእነዚያ ጀግኖች ሰማዕታት፡ እየራሳችሁን፡ ለመሥዋዕትነት ማቅረብ አለባችሁ:: "እንዴት ነው፡ እየራሳችንን፡ እንደእነዚያ ጀግኖች ሰማዕታት፡ ለመሥዋዕትነት የምናቀርበው?" ብትሉኝ፡ እንዲህ ብዬ እመልስላችኋለሁ:-

“አገራችንንና ወገናችንን፡ ለዚህ ጥፋት የዳረገው፡ ይህ፡ የሰዎች ሥርዓት፡ ቀድሞ እንደነበረው፡ አኹንም፡ “ዝም ብሎ ይቀጥል!” ከማለት ይልቅ፡ “በየዘመናቱ እያመረቀዘ፡ እንዲህ፡ ተደብቆና ተሠውሮ፡ በሥቃይ የሚያጥመነምነንና የሚያሽመደምደን ነቀርሳማ ደዌ፡ ከቶ ምንድር ነው?” ብላችሁ፡ ደዌዉን ፈልጋችሁ በማግኘትና እውነቱን በገሃድ በመመስከር፡ ፍጹም የኾነውን ዘለዓለማዊዉን ፈውስ ልታመጡ ይገባችኋል፡፡” እነዚያ ምሳሌዎቻችሁ ጀግኖች ሰማዕታት ያደረጉት፡ ይህን መኾኑን፡ ገድላቸው፡ ዛሬም፡ እነሆ፡ እየጮኸ ሲናገር ትሰሙታላችሁ፡፡ የዚህን ጥያቄ፡ ዝርዝር መልስ ከመጻሕፍቴ ልትመለከቱ ትችላላችሁ፡፡ (ማቴ. 3፥ 1-0፤ 04፥ 1-02፤ 05፥ 3-9፡፡ የሐዋ. 7፡፡ ዳን. 3፤ 6፡፡)

6ኛ፡- ከዚህ ቀጥዬ፡ “ለንቡርዕድ ኤርምያስ ከበደ እርማት መልስ” በሚል ርእስ፡ አባሪ አድርጋችሁ ለላካችሁት፥ ለደቀ መዝሙር በርሄ ተስፋ መስቀል ጽሑፍ፡ የሚከተለውን አስተያየት እሰጣለሁ፡- (ትክክለኛው አጻጻፍ “ንቡረ እድ” መኾኑን ማስተዋል ነው፡፡)

ሀ. እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ከእግዚአብሔር በምርቃትና በበረከት፥ በፍቅርና በስምምነት የተቀበልነው፡ ኪዳንን እንጂ፡ ሕግን አይደለም፤ ያም ኪዳን፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በኖኅ፥ በመልከ ጼዴቅ፥ በአብርሃም፥ በሙሴና በዳዊት አማካይነት ተላልፎ፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም የተፈጸመው ነው፡፡ የአገዛዝ ኀይል ያለውን ሕግን የተቀበሉት፡ አሕዛብና እሥራኤል ናቸው፤ አሕዛብ፡ በሕሊና ብቻ፥ እሥራኤል ግን፡ በጽሕፈት ጭምር፡፡ መልስ ሰጪው፡ ከባዕዳን መምህራን ሠርጎ በገባው ይትበሃል በመጠቀም፡ “ሕገ ልቦና፥ ሕገ ኦሪትና ሕገ ወንጌል” ላሏቸው የግዳጅ ድንጋጌዎች፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ቢበዛ፡ የምንጠቀመው፡ “ኪዳነ ልቦና፥ ኪዳነ ኦሪትና ኪዳነ ወንጌል” በሚል ስያሜ ነው፡፡ የጣዖት አምላኪው፡ የታራ ልጅ የነበረው፡ አብርሃም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ ተምሮና ተባርኮ፡ ለእግዚአብሔር የግርዛት ቃል ኪዳን እስከበቃበት ቀን ድረስ፡ ቀድሞ “ዕብራውያን”፥ ኋላም “እሥራኤል” የተባሉት፡ የእርሱ ወገኖች ጭምር፡ እንደአሕዛብ፡ ሕገ ልቦናን የተቀበሉት፡ በተፈጥሮ ብቻ ሲኾን፡ ኢትዮጵያውያን ግን፡ በቃል ኪዳን መኾኑን፡ የኢትዮጵያውያን ዜና መዋዕል፥ እንዲሁም፡ ከመልከ ጼዴቅ የተገኘችው፡ የንግሥተ ሳባ ሃይማኖትና ምግባር ያረጋግጣል፡፡

እሥራኤል፡ ሕገ ኦሪትን የተቀበሉበትን ኹኔታ፡ ኢትዮጵያውያን የሚቆጥሩት፡ እንደሚያሳፍር ግብር እንጂ፡ እንደሚያኮራና እንደሚያስመካ አድርገው አይደለም፤ ስለዚህ፡ ለምንድር ነው፡ ኢትዮጵያውያን፡ ይህን ድርጊትና ዝክረ ነገሩን፡ የእነርሱ አድርገው ሊወስዱት ፍላጎት የሚኖራቸው? ፍላጎቱ፡ ቀድሞም፡ አልነበራቸውም፤ ዛሬም የላቸውም፤ ወደፊትም አይኖራቸውም፡፡ እሥራኤል፡ በሲና ተራራ ሥር ሠፍረው ሣሉ፡ በመለኮታዊ ክንዱ፡ ያን ያህል የታዳጊነት ቸርነቱን፡ በግብፅና በምድረ በዳ ላደረገላቸው፡ ለኢትዮጵያ አምላክ፡ ለእግዚአብሔር የመለሱለት ውለታቢስነት፡ እንዴትና ምን እንደነበረ፡ ሙሴ በጻፈው የኦሪቱ መጽሓፍ ውስጥ በግልጽ ይነበባል፤ ታቦተ ሕጉን ያስገኘው፡ ያ፡ የእሥራኤል፡ የ“ውለታቢስነት” ሥራ፡ ከቶ ምንድር ነበር? ክህደትና ጣዖት አምላኪነት፥ ዓመፅና አመንዝራነት አይደለምን? ታዲያ፡ ይህን ታላቅ ኃጢኣት፡ ኢትዮጵያውያን እንዴት እንደሚፈልጉት አድርጎ ለማሳየት ይሞከራል? ይህን የመሰለውን ሙከራ ማድረግ፡ ኢትዮጵያውያንም፡ በዚያ ታላቅ ኃጢአት እንደተሳተፉበት ለማስቆጠር ከሚውጠነጠነው ሰይጣናዊ ሤራ ጋር መተባበር ይኾናል፤ *“ንግሥተ ዓዜብ፡ ይህን (የእሥራኤልን) ትውልድ ትፋረደዋለች!”* የሚለውንም የጌታ ቃል ማስተሓቀር ይኾናል፡፡

ታቦተ ሕጉን ያስገኘውን፡ ያን፡ የእሥራኤልን የ“ውለታቢስነት” ሥራ፡ ኢትዮጵያውያን ያፍሩበታል፥ ይጸየፉታል እንጂ፡ አይፈልጉትም፡፡ እግዚአብሔር፡ ዓሠርቱ ትእዛዛትን የያዘውን ሕግ፡ ለአምልኮ ፍላጎታቸው በተስማማ መልክ፡ በድንጋይ ላይ ቀርጾ የሰጠው፡ ለእሥራኤል እንጂ፡ ለኢትዮጵያውያን አለመኾኑ፡ በይፋ የታወቀ ነው፤ ዓሠርቱን ቃላትማ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ቀደም ብለው፡ በኪዳነ ልቦና ተቀብለዋቸውና አምነውባቸው፡ በእውነትና በመንፈስ መመለክን የሚወድደውን ፈጣሪያቸውን፡ በዚያ ሥርዓት ሲያመልኩባቸው ኖረዋል፡፡

እሥራኤል፡ ያንኑ ታቦተ ሕጉንም ቢኾን ያገኙት፡ ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶና ልጆችን ወልዶ፥ ስለአምልኮተ እግዚአብሔርና ስለዓሠርቱ ቃላት፡ ከአማቱ ከዮቶርና ለሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ካህናት ተምሮና አውቆ፡ በኢትዮጵያ፡ ለአርባ ዓመታት በመኖር፡ ኢትዮጵያዊነትን በተቀበለው በሙሴ አማካይነት መኾኑ ተጽፏል፤ በእሥራኤል ዘንድ የነበረውን ሃይማኖትና ምግባር የሚያውቀው እግዚአብሔር፡ ሙሴን፡ ለዚያ ታላቅ ተልእኮ መርጦ፡ ወደግብፅ የሰደደው፡ የእነርሱ ብቅዓት አገብሮት ሳይኾን፡ ስለደጋግ አባቶቻቸውና እናቶቻቸው ሲል መኾኑ ተነግሮኣል፤ የኋላ ኋላም፡ እሥራኤል፡ ያንኑ፡ የታቦተ ሕጉን ግዳጅ፡ በሃይማኖትም ኾነ በምግባር መፈጸም አቅቷቸው፥ እንዲያውም፡ ወደለመዱት ክህደታቸው፥ ዓመፃቸውና አመንዝራነታቸው ተመልሰው፡ ያንኑ የቀድሞውን ሰይጣናዊና ባዕድ አምልኳቸውን በመቀጠላቸው፡ እነርሱ፡ የኃጢኣታቸውን ዋጋ ሲቀበሉ፡ አማናዊቷ ታቦት፡ ድንግል ማርያምና አማናዊው ጽላት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰውነት፡ ሕያዋን ኾነው እስኪገለጹ፡ ድረስ፡ ታቦተ ሕጉ፡ ወደኢትዮጵያ መጥታ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በአደራ ተጠብቃና በሚገባ ስትመለክ እንድትኖር የተደረገበትን፡ የእግዚአብሔርን ድንቅ ጥበብና የኢትዮጵያውያንን እውነተኛ ምንነት መዘንጋት አይገባም፡፡

በ. የቅዱስ ጴጥሮስን ሕይወት ምሳሌ በማድረግ፡ ኢትዮጵያዊ ስሜትን፡ ከእውነት ጋር ሳያጋጩ (ሳይደባልቁ) መቀበል፡ አዋቂነት ስለመኾኑ፥ ደግሞም፡ ስሜት አለቦታው ሲገባ፡ ብዙ ነገሮችን ሊያናጋ እንደሚችል ስለመረዳት፥ ክርስትና ወደኢትዮጵያ ስለመግባቱም፡ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈውን፡ በረጋና በሰከን ስሜት ማመኑ፡ ብልህነት ስለመኾኑ፡ በመልስ ሰጪው በኩል የተሠነዘረው ትችት፡ ምን ለማለት ይኾን? ቀዳሚ የኾነችው ኢትዮጵያና ቀዳማውያን የኾኑት ኢትዮጵያውያን፡ ከፈጣሪያቸው ያገኙትንና እነርሱም በቃል ኪዳን ጠብቀው ያኖሩትን፡ ይህንኑ ቀዳማዊነታቸውን በሚመለከት፡ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በተመሠረተ እውነት ማስረዳት፥ መናገርና መጻፍ፡ እንዲህ ያለውን ትችት ያስከትላልን? ያውም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ከሚል ግለሰብ? ምስጋና ይድረሰውና፡ ከራሱ ከጌታ ጀምሮ፡ ከላይ፡ ስማቸውን የጠቀስኋቸው፥ ደግሞም፡ ሙሴና ቅዱስ ጴጥሮስ፥ እነርሱንም የመሰሉት ነቢያትና ሐዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት፡ የተናገሩትና ያስተማሩት፥ የሰበኩትና የጻፉት፡ "እስመ ቅንዓተ ቤትከ በልዓኒ!" የሚለውን፡ የመንፈስ ቅዱስ ቃል ተከትለው፡ በሃይማኖታዊ ቅንዓት መኾኑ ቀርቶ፡ በስሜት ነበር ማለት ነውን? ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያውያን፡ የተባለውን ኹሉ፡ ፍልስጥኤማዊው እስላም፡ "ያሲን ዓረፋት"፡ ስለኢየሩሳሌም ካሉት ጋር በማነጻጸር፡ ከመልስ ሰጪው፡ የተሠነዘረውን፡ ሌላ ትችት፡ በአንክሮ ይመለከቷል፡፡

ገ. ለመኾኑ፡ ደቀ መዝሙርነት እንዲህ ነውን? እንኳንስ፡ "ደቀ መዝሙር ነኝ!" የሚል ይቅርና፡ ሌላ ማንኛውም አንባቢ ቢኾን፡ ለተጻፈለት፥ ወይም፡ ለቀረበለት ጥያቄ፡ መልስ ለመስጠት፡ እንደእናንተ፡ እንደእውነተኞቹ ደቀ መዛሙርት አቋም፡ በቅድሚያ፡ ከጥያቄው ባለቤት፥ ወይም ከምንጩ ጠይቆ የመረዳት ፍላጎት ሊኖረው አይገባምን? በቃል፥ ወይም፡ በጽሑፍ ጠይቆ መረዳት በይፈለግ፥ ወይም፡ ባይቻል እንኳ፡ አስቀድሞ፡ የዚያን የጠያቂውን ሰው አሳብ፡ በዝርዝር አውቆ፥ ወይም፡ መጻሕፍት ካሉት፡ እነዚያን በሚገባ አንብቦ፡ ትክክለኛውን መረጃና ግንዛቤ ማግኘት፡ አግባብ አይኾንም ኖርዋልን? "ደቀ መዝሙር" ተብሎ፡ እንደደቀ መዝሙር፡ የመጻፍን ሥነ ሥርዓትና ሥነ ምግባር ካልተከተሉ፡ "ደቀ መዝሙር፡ እንደመምህሩ መኾን ይበቃዋል!" የሚለውን፡ የታላቁ መምህራችንን መመሪያ ማስተሓቀር አይኾንምን?

ዷ. እኔ፡ በኢትዮጵያዊነቴ፡ ከፈጣሪዬና ከቅድስት እናቱ በተቀበልሁት አደራ፥ ከዚህ የተነሣም ባለብኝ ኀላፊነት፡ ቀደም ብዬ፡ "ኢትዮጵያዊው፥ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" እና Ethiopia: The Classic Case፥ በቅርቡም፡ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት" በሚል፡ ተከታታይ ርእስ ሥር፡ "አንደኛ መጽሐፍ"፥ "ኹለተኛ መጽሐፍ" እና "ሦስተኛ መጽሐፍ" በሚሉ አርእስት፡ መጻሕፍትን አዘጋጅቼ፥ እነዚህ፡ ኢትዮጵያዊ መልእክትን የያዙ ድርሰቶችም፡ በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት ታትመው ወጥተው፡ ለሕዝብ ሊሠራጩ የበቁት፥ ለእናንተም፡ እንዲደርሷችሁ የተደረገው እኮ፡ ያለምክንያት አይደለም፤

ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያውያን፥ ወይም፡ ስለራሱ ስለኢትዮጵያዊነት ሳይቀር፡ ምንም የማያውቀውን፥ "አውቋል!" ቢባልም፡ ያን እውቀቱን ያገኘው፡ በባዕዳን ተንኰል፡ ኾነ ተብሎ፡ በተሳሳተ መንገድ፡ በመኾኑ፡ እነሆ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በታላቅ የጥፋት ማዕበል ውስጥ ወድቆ፡ ሲንገላታ የሚታየውን፡ የዛሬውን የኢትዮጵያ ትውልድ፥ መልስ ሰጪውንና የመሰሉትን ጨምሮ፡ እውነተኛ ማንነቱን እንዲገነዘብ በማስቻል፡ ወደጤናማ ህልውናው ለመመለስ እኮ ነው:: በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ በግዙፋን ወራሪዎች፡ ሲፈጸም የኖረውን ጥቃት መክቶ ለመመለስ ቢቻልም፡ ረቂቅ የኾነውን ለመቋቋም ሳይሞከር በመቅረቱ፡ ቀደም ብሎ፡ በእሥራኤላውያን፥ በመካከሉም፡ በግብፅ ኦርቶክሳውያን፥ ኋላም፡ በዓረባውያንና ዛሬም፡ በዓለማውያን የተካኼደውንና እየተካኼደ ያለውን ደባና ጥቃት መክቶ ለመመለስ፡ ለኢትዮጵያዊው ትውልድ ያዳገተው ኾኖ፡ ይኸው፡ በገሃድ ይታያል::

ይኹን እንጂ፡ በዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ዘንድ፡ ይኸውም፡ በቤተ ሕዝቡም፥ በቤተ ክህነቱም፥ በቤተ ምልክናውም ዘንድ፡ ሰፍኖና ዐይሎ የሚታየው፡ ይህን የመሰለው፡ የባዕዳኑ ረቂቅ የጥፋት ኃይል ቢኾንም፡ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚመሰክሩት፥ የዘመናችንም እውነታ እንደሚያረጋግጠው፡ በዚህ መልክ፡ በግዘፍ ኾነ በረቂቅ የሚመጡት፡ የርኩሳን መናፍስት ኾነ የፍጡራን ኃይላት፡ ምንጊዜም፡ እነርሱ፡ በየራሳቸው ተንኰል፡ እየራሳቸውን ያጠፋሉ እንጂ፡ እግዚአብሔር፡ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን ጋር፡ በቃል ኪዳን የመሠረተውንና ያጸናውን፡ የተቀደሰ ዘለዓለማዊ ሥራውን፡ ሊያነዋውጹትና ሊያፈርሱት ቀርቶ፡ ሊነኩት እንኳ አልተቻላቸውም፤ አይቻላቸውምም::

7ኛ:- እኔና እኔን የመሰሉት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በየትኛውም ቦታና ኹኔታ፡ የምንኖረው ሕይወትና የምናበረክተው አገልግሎት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ለኾነችው ኢትዮጵያ ነው፤ ከመጀመሪያው አንሥቶ እስከዛሬ፡ የዚች ኢትዮጵያ፡ መመሪያና መተዳደሪያ ይኾናት ዘንድ፡ ከፈጣሪዋ፡ በቅዱሱ ኪዳን የተሰጣት ሥርዓት አለ፤ ያም ሥርዓት፡ በተለይ፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው መጽሓፌ መጨረሻ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል:: እያንዳንዱን ሰብአዊ ፍጡር፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ "እውነተኛ" ኢትዮጵያዊ/ት የሚያሰኘው፡ በሥጋም፥ በነፍስም፥ በመንፈስም፡ ያን ሥርዓት ተከትሎ የሚኖር ለመኾኑ፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም መንበር ፊት ቆሞና ሰግዶ፡ የምስክርነት ቃሉን፡ በይፋ የሰጠ እንደኾነ ነው፤ *"በሰው ፊት የሚመሰክርልኝን ኹሉ፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ!"* የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ በዚህ ሥርዓት፡ እውንነትንና ፍጹምነትን ያገኛል:: ለዚህ ሥርዓት፡ ሃይማኖታዊና ምግባራዊ አቋም ደግሞ፡ መሠረቶቹ፡ በዚህ ደብዳቤ፡ ከምስክርነቱ ቃል ጋር አያይዤ የላክኋቸው፡ "የኢትዮጵያውያን የሃይማኖትና የቃል ኪዳን፥ የምስጋናና የሰላምታ ጸሎታት" ናቸው::
(ዘጸ. #2፤ #4፥ 1-9:: መዝ. ^8፤ 9-0:: ማቴ. 0፥ @4-@5፤ #2-#3፤ 02፥ $2::)

እግዚአብሔር፡ ጥንት፡ በኪዳነ ልቦናም ኾነ በመካከሉ፡ በኪዳነ ኦሪት፥ በመጨረሻም፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ አማካይነት፡ ለፍጥረቱና ለሰው ልጆች ያደረገው ቸርነቱ የተገለጹበት ሕያዋን ሥራዎቹ ኹሉ ተሰባስበውና ተከማችተው፡ በመዘክርነት እንዲቀመጡ፥ በባለደራነት ተጠብቀውና ተከብረው እየተሠራባቸው እንዲኖሩም ያደረገው፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ዘንድ መኾኑ፡ ተረጋግጦ ይታወቃል። ይህም የኾነው ያለምክንያት አይደለም፤ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ ለዚህ ጸጋና ክብር ያበቃቸው ምክንያት፡ እውነተኛዋን የእግዚአብሔር አምልኮት የሚፈጸምባትን ሃይማኖትና እርሱ የሠራትን፡ የቀናችውን ምግባር ፈልገውና ወድደው ስለመረጡ ብቻ ነው።

እንዲህ፡ በእግዚአብሔር ስለተመሠረተውና ከእርሱ፡ በቃል ኪዳን ስለተገኘው ኢትዮጵያዊነት፡ ይህን የመሰለውን ጥንቃቄ ማድረግ፡ እጅግ ያስፈለገበትም ምክንያት፡ ግልጽ ሊኾንላችሁ ይገባል፤ ይኸውም፡ “ኢትዮጵያዊ ነኝ!” ብሎ፡ በኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና ውስጥ የሚገኘው፡ እያንዳንዱ ግለሰብ፡ እንኳንስ፡ ምንም በማያውቀው፡ በደካማው ፍጡር ዘንድ ቀርቶ፡ በፈጠረው፡ በእግዚአብሔር ዘንድም እንኳን ቢኾን፡ ምንነቱንና ማንነቱን፡ በእውነተኛነትና በእርግጠኛነት ለመለየት ካልተቻለበት ጊዜ ላይ የደረስን በመኾናችን፡ ያ ግለሰብ፡ ሕዝባዊም ኾነ ካህን፥ ወይም ምሉክ፡ በእውነትና በእርግጥ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ መኾኑን፡ በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ እርስ በርሳችን፡ በግልጽ ተዋውቀን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ ከቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ጋር በመካከላችን እንዲገኝ ሊያደርግ የሚችለውን፡ እውነተኛ መተማምንን ለማበርከት ነው።

ስለዚህ፡ በዚህ አገልግሎት ውስጥ ለምንገኝ ኹሉ፡ በማኅበራችሁም ኾነ በመጽሔታችሁ ውስጥ አባል፥ ወይም፡ ተባባሪ ለመኾን፡ በእናንተ በኩል፡ ይህን፡ የሥርዓታችንን መመሪያ፡ በቅድሚያ ልትፈጽሙ የሚያስፈልግ መኾኑን ልገልጽላችሁ እወድዳለሁ።

በዚህ አጋጣሚ፡ “አምላከ ኢትዮጵያ፡ ልዑል እግዚአብሔር፡ ኢትዮጵያውያንን ኹሉ፡ በያለንበት፡ ከዘመነ ማቴዎስ ወደዘመነ ማርቆስ፡ በደህና አሸጋግሮ፥ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ስም የተጠራች፡ አገራችንንም ጠብቆ፡ የ7ሺ4)(8ኛውን ዓመት የነጻነት ህልውናና የ1ሺ9)(8ኛውን ዓመት፡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ቀን በዓላችንን ለማክበር ለበቃንበት፡ ለአዲሱ፡ መስከረም 1 ቀንና ለ09)(8 ዓመተ ምሕረት፡ እንኳን አደረሰን!” እላችኋለሁ።

---

ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ
የአገልግሎቱ ተጠሪ

አባሪ፡-

5 (አምስት) ገጾች።